# አባሪ

እ.ኤ.አ መስከረም 20 ቀን 2016 በኒውዮርክ ከተማ 71ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በተዘጋጀበት ወቅት በኢፌዲሪ መንግስት ቃል የተገቡ Pledges የሚከተሉት ናቸው፡፡

**አንደኛ፡-** ኢትዮጵያ Out of Camp Policy በሚል የተወሰኑ ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ እንዲኖሩ ስትፈቅድ ቆይታለች ፡፡ በመሆኑም ይህንን ዕድል ለሁሉም ስደተኞች በማስፋት ከጠቅላላ ስደተኛው አስር በመቶ ያህል ለሚሆኑ ስደተኞች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸትና ለወደፊቱም አቅም በፈቀደ መጠን የተጠቃሚዎችን ቁጥር ለመጨመር፣

**ሁለተኛ፡-** የአገሪቱ ሕጎች በሚፈቅዱት መሠረት ስደተኞችና ቋሚ የመኖሪያ መታወቂያ ያላቸው የውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ እንዲያገኙ ለማድረግ፣

**ሦስተኛ፡-** ብቁ የሆኑትን ቅድሚያ በመስጠት በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የተመረቁ ስደተኞችን ለውጭ ዜጎች በተፈቀዱ የሥራ መስኮች ላይ እንዲሳተፉ የሥራ ፈቃድ ለመስጠት፣

**አራተኛ፡-** የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን እና ያለምንም መድልዎ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ስደተኞች ተደራሽ ለማድረግ፣

**አምስተኛ፡-** ከውጭ በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ በመጠለያ ጣቢያ የሚኖሩ ስደተኞችና በአካባቢው የሚኖሩ ዜጎች በጋራ በመስኖ ሥራ ሰብል በማምረት ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ፣

**ስድስተኛ፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ ከ20 ዓመት በላይ በስደተኝነት የቆዩ ከ13,000 በላይ የሚሆኑ ስደተኞች ከአገሪቱ ሕዝቦች ጋር ተዋህደው የሚኖሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣

**ሰባተኛ፡-**ኢትዮጵያ የስደትና ፍልሰት መነሻ፣ መሸጋገሪያና መዳረሻ አገር መሆኗን ታሳቢ በማድረግ ይህንኑ ለመቅረፍ የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶችን በማሳደግና በማስፋፋት ለዜጎችና ለስደተኞች ተጨማሪ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣

**ስምንተኛ፡-** በአገሪቱ ሕጎች ማዕቀፍ ውስጥ እንደክትባት፣ የሥነ-ተዋልዶ ትምህርት፣ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ እና የመሳሰሉ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በማጠናከርና በማስፋፋት ለስደተኞች ለማቅረብ፣

**ዘጠነኛ፡-** ስደተኞች የባንክ የሒሳብ ደብተር መክፈትን፣ የመኪና መንጃ ፈቃድ ማግኘትን እና ሌሎች ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው የውጭ ዜጎች የሚያገኟቸው አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑና ስደተኛ ሕፃናት የልደት የምስክር ወረቀት የሚያገኙበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት ቃል ተገብቷል፡፡